# ምነው በኢሕአፓ ላይ ጩኸት በረከተሳ?

ማሜ መንበረ

ጩኸቱን አጠቃለን እስቲ እናቅርበው፤

- የመለስ ዜናዊ የይፋ ደጋፊ የነበረ ፤ በወያኔ መንግስት መዋቅር ገብቶ ስልጣን የተካፈለ ፤ የአማራ ሕዝበ ከየት ወዴት ብሎ አሳዛኝ የጎጠኞች ደጋፊ መፅሀፍ ብጤ ፅፎ የነበር ግለሰብ ዛሬ በምን መንገድና ለምን ለምንለው አጥጋቢ መልስ ሳይሰጥ የተቃዋሚ አንጃ መሪ ነኝ ብሎ በመሰየም ሰሞኑን ስለ ኢሕአፓ በአንድ የዋሺንግተን ቴሌቪዥን ሲጠየቅ ኢሕአፓማ ደምሳሽ (አጥፊ) ነው ብሎ ሲመልስ አድምጠናል። ይህ ግለሰብ በዚህ ድርጅት ድሮ አባል ነበርኩ ቢልም የአመራር አባሎችን በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ በመኪና ከማመላለስ ሌላ ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ተሳትፎ አልነበረውም ብለው የሚያውቁ አጋልጠውታል። ወደ አሲምባ ዘለቅኩ ሲልም ወያኔን አግኝቶ በዚያው ወደ ሱዳንና እንግሊዝ አቅንቶ በዚያው በወያኔ ዙሪያ በለንደን ሲሰራ የከረመ ሲሆን ዛሬም ቢሆን ቅንጅትን በማዳከም የሚያደርገው ሁሉ ለወያኔ እየጠቀመ ነው ተብሎ የሚታማ ነው። ዶክተር አበበች የተባሉ ኢትዮጵያዊት ምሁር ይህን ግለሰብ በቃለ መጠይቅ በፓል ቶክ በሰፊው አጋልጠዋል። ግለሰቡ በጋብቻ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ገመዶችም ካለው ገዢ ቡድን ጋር የተሳሳረ ነውም ተብሏል።
- ግለሰቡ በተወሰነ ወቅት የአንድ የተግባር ቢባልም የአፍራሽ ኮሚቴ አባል ነኝ ብሎ ኢዴሀህ እንዳይመሰረት መሰል አፍራሾችን (አሰፋ ጩቦ፤ ዓለም እሸቴ፤ወዘተን) ኮልኩሎ በአፀያፊ መንገድ ሳይቀር የታገለና ጥረቱ የከሸፈበት፤ ቀደም ሲልም ለእነ ፖል ሄንዚና ሌሎች የወያኔ አማካሪዎችና ፀረ ወያኔ ታጋይ ድርጅቶችን ለሚያጠቁ ግለሰቦች መድረክ የሆነ መፅሄት ሲያካሂድ የቆየ፤ አፍራሽና የባዕድ ቅጥረኛ ተብሎ የተወገዘ ፡አድብቶ ቆይቶ በቀድሞ መፅሄቱ ስም ድህረ ገፅ ከፍቶ የቅንጅት ደጋፊ ነኝ በሚል ቅንጅትን ያባላና የከፋፈለ (በዚህ መስክ ስልጠና ሳይሰጠው አልቀረም)፤ በሀገር ቤት የሚንቀሳቀሱትንም የተወሰኑትን ያስበላ፤ ፀረ ሻዕቢያ ነኝ ሲል ቆይቶ ከመ ቅፅበት ደግሞ የሻዕቢያና ኦነግ ጭፍን ደጋፊ በመሆን ዛሬ ደግሞ (የዘሬን ብተው እንደተባለው) ኢሳይያስ በኢትዮጵያ አንድነት ያምን ነበር፤ አሁንም ያምናል ብሎ የሻዕቢያ ቅጥረኛነቱን ያጋለጠ መሰሪ ግለሰብ ለፀረ ኢሕአፓ ፅሁፎች በድህረ ገፁ ዋና አሰራጭ ሆኖ ድንገት ብቅ ብሏል።
- ሌላው ግለሰብ ደግሞ ክህደት የለመደበት፤ በኢሕአፓ ሰራዊት ችግር ሲፈጠርና በታኞች እነ ተፈራ ዋለዋ በረከተ ስምዖን ወደ ወያኔ ሲያመሩ እሱ ወደ ደርግ የሸመጠጠ ፤ ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላትን መስብስብ በሚል ሽፋን ኢሕአፓን ሊያጠፉ ፎረም 84 የተባለ ተቋም ሲመሰርት የዚሁ አባል ሆኖ የሰራና በዳዊት ዮሀንስ ተመልምሎ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለውን የሰራተኛ ማህበር እንዲመራ የተመደበ ነው። በዚሁ ቦታ ሳለ የመቀጠሉ ጉዳይ አላመች ሲለው ዛሬ እያወገዘ ያለውን ኢሕአፓን ተማፅኖ ወደ ኬንያ የተሰደደና እዚያም በዚሁ ድርጅት እርዳታ የቆየ፤ ከዚያም ወደ ሆላንድ አምርቶ እንደገና በዚሁ ድርጅት አባላት ሲረዳ የቆየ ግለሰብ ነው። መኮፈስ ቀፎነትን ይደብቃል ብሎ የገመተው ይህ ግብዝ እያደር በአልባሌና ተልካሻ ጠባዩ ሲጋለጥ፤ ግለሰቦች ከአዲስ አበባ የሰጡትን ገንዘብ በልቶ አልመልስ ሲል፤ ባለቤቱን እየደበደበ ለመለያየትና ፍች ሲደርስ፤ በሰራተኛ ማህበር ስም የተሰበሰበን ገንዘብ ማዋራረድ ሲያቅተው ለሁሉም ጉድለቱና ጥፋቱ ኢሕአፓን መክሰስ ልምዱ የሆነ የሰው መሳቂያና መሳለቂያ ነው። ግለሰቡ ከጥቂት ዓመታት ጀምሮ በአምስተርዳም ባለው ቀንደኛ ወያኔ ሙሉጌታ አስመላሽ ተቀጥሮ ለወያኔ በይፋ እየሰራ ያለ ነው። ታዲያ ከዚህ አዘቅትና ከተኛበት ማን ቀስቅሶ አወጣው ዛሬ?ለምን?
- ሌሎች በሰሞኑ ብሶባቸው በኢሕአፓ ላይ የሚያጓሩት ደግሞ በተወሰነ ፓልቶክ ውስጥ የወያኔና ደርግ--ኢሰፓ "ቦጅ ቦጅ" ሆነው ተጨባጩን ሁኔታ እንወያያለን ቢሉም ደም እያቃዣቸው በኢሕአፓ ላይ መዝመቱን፤መለፍለፉን የመረጡ ናቸው። በመጀመሪያ የጠቀስነውን ግለ ሰብና ቡድኑን እንደግፋለን ቢሉም በዚህ ውስጥ ያሉት ወያኔዎች በአብዛኛው ስራቸው ቅራኔን ማባባስ ከፋፋዮችን ማወደስ ነው።

ጩኸቱ ለምን ዛሬ የሚለው ጥያቄ ምላሽን የሚፈልግ ነው ግን ጩኸታቸው አዲስም ሀቀም አይደለም፡፡ ካለይ በቱቀሰው ድህረ ገፅ ላይ ረጅም ፅሁፍ ያቀረበውና የነጠርኩ ፀረ ትግሬ ነኝ አውቁኝብሎ ሊኩራራ የከጀለወ ግለሰብ ኤኤፍዲ ወይም ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተባለው ስብስብ በተወለደለ ማግስት በመሰናበቱ ወይም ዋጋ ቢስ ሆኖ በመገኘቱ ለዚህ ውድቀት ተጠያቂ ኢሕአፓ ነው ሊል ይፈልጋል፡፡ ለማወናበድ መቸም ጥራዝ ነጠቅነት አንድ መሳሪያ ነውና አይታወቅብኝም በሚል የመያውቀውን የካምፑቺያ ቀይ ክሜሮች ስም አንስቶ ህወሓትና ኢሕአፓ አንድ ናቸውም ቀይ ክሜርም ናቸው ሊል ሞክሯል፡፡ ልብ ሳይገዙ ነግር አያበዙ ቢባልም እነ አያ ውድቀታቸውን ለመሸፈን በኢሕአፓ ላይ መዝመቱን መርጠዋል፡፡ ዶክተር ታየ ወልደ ሰማያትም የቅንጅት አንዱ ወገን ሊቀመንበር ሆነው ሲመደቡ ይህም የኢሕአፓ ሻጥር ተብሎ፤ ዶክተር ታዬ ራሳቸውም በኢሕአፓነት በዘፈቀደ “ተመልምለው” በተጠቀሰው ፓልቶክ በኢሕአፓ ላይ ብዙ ውርጅብኝ ተደረገ ፡፡ ለቅንጅት መከፋፋል ሆነ ለአንጃዎቹ አርስ በርስ መናከስ፤ ለኤኤፍዲ ድጋፍ ማጣት ሆነ መሞት ኢሕአፓ ተጠያቂ አይደለም፡፡ ድርጅቶቸና ቡድኖች የራሳቸው ሂደትና ይዞታ ሲከብድና በቀውስ ሲናጡ ሁሌም ኢሕአፓን በማውገዝ ድክመታቸውን ሊሸፍኑ ቢነሱ በክሳቸው ከመርካት ባሻገር ድርጅታቸውን አያድኑም፡፡ ኢሕአፓ ግን ለሰበብ ከጠቀማቸው ቀጥሉ ባይ መሆኑ ይገመታል፡፡

የደርግና የወያኔ የይፋም ሆነ የስውር አባላትና ደጋፊዎች ደግሞ የኢሕአፓን ታሪክ መበረዝ መከለስና ሰማዕትን ማንቋሸሽ የሚቀናቸው ተልዕኮአቸውን ለመወጣትና የክህደት ማንነታቸውን ለመደበቅ ነው፡፡  ጥይት በሚንጣጣበትና ጀግኖች በሚፎክሩበት አውድማ ሊውሉ ቀርቶ የባሩድ ሽታ ትላንት ከወዲያ በዚህ ነበር በተባለበት ያላለፉና ሊያልፉም የማይደፍሩ እነዚህ ወኔ ቢሶች ለምሳሌ ስንት ገድል የሚተረክላትን ጀግና፤ ፎረም 84 ሳይሆን በወያኔ እስር ቤት ገብታ የነበረችውን፤ ወያኔን ምህረት የጠየቀች ሳይሆን በራሱ ህዝብ ባዳመጠው መድረክ አዋርዳና የድርጅቷን ስምና ክብር አስጠብቃ ታሪከ የፃፈችውን አያልነሽንም በፓል ቶካቸው ሊሰድቡ ሞክረዋል፡፡ ወያኔን መቃወም ሳይሆን ሚስቱን መደብደብና ለወያኔ ቅጥረኛ መሆን የቀናው ከላይ የጠቀስነው ሌላ ግለሰብ ደግሞ ስዩሜ ከበደና ሌሎች ሰማዕትን ሊያንኳስስ ሞክሯል፡፡ ስዩሜ ከበድ የሀገሬ ፖለቲካ ጉዳየ ተወሳሰበ አስቸገረ--አስፈራ ብሎ ወደ አሜሪካ ስደት የሄደ ሳይሆን ሀገርን ለማዳን ከአሜሪካ ወደ ሀገር የተመለሰና በህቡዕ የኢሕአፓ ስራ የተሳተፈ ጀግና ወጣት ነበር፡፡ ስዩሜ ወደ ሀገር ከመመለሱ በፊት ወደ አሲምባ ካቀኑት የኢሕአሠ መስራቾች ጋር የሰለጠነ ስለነበረም ኢሕአፓ በከተማ ጦርነት ታውጆበት ጥቃት ሲሰነዘርበት የመከላከያ እርምጃ ሲወስድ ስዩሜ በማሰልጠንም ሆነ በተግባር በመሰማራት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረገ ጀግና ነው፡፡ ከተካፈለባቸው ተልዕኮዎች አንዱ አምባገኑን መንግስቱን ለመግድል በተደረጉ ሙከራዎች መሆኑ ለደርግ አጫፋሪዎችና መንጌ መንጌ ባዮች ያስቆጣ ይሆን እንጂ በህዝብ ዘንድ የሚከበርና ለጀግናው ስዩሜ አድናቆትን ያስከተለ ነው፡፡ ጀግናው የኢሕአፓ ልጅ ስዩሜ በፒያሳ አካባቢ አንድ የተዚያን ጊዜ ባንዳ ጠቁሞበት ከደርግ ነፍሰ ገዳዮች--የአንዳንድ የዛሬ ፓልቶክ ዕድምተኞች ጓደኞች--ጋር ተቷኩሶ የተሰዋ ጀግና ነው፡፡ ትናንሽ ሰዎች፤ ከታሪክ አንፃር ኢምንቶችና ቁንጮች ታላላቅ ሰዎችንና ጀግኖችን በዘለፉ ቁጥር ቦታና ዋጋ ያገኙ እየመሰላቸው ሁሌም ተንጠራርተውና ተፍጨርጭረው ለማዋረድ ይጥራሉ፡፡ ውርደቱ ግን የራሳቸው ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡

የጩኸቱ አንድ ይዘት ደግሞ ኢሕአፓ ፀረ ወያኔ ግንባር እንዳይመሰረት ያደርጋል የሚል ነው፡፡ በመሰረቱ ፀሀፊው ፀረ ወያኔ ይበል እንጂ ከፅሁፉ ይዘትና መንፈስ ፀረ ትግሬ ሊል መፈለጉ ግልጥ ነው፡፡ ኢሕአፓ ፀረ ትግሬ የሆነ ግንባር መመስረቱን መቃወም ብቻ ሳይሆን ከተመሰረተም የሚታገለው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ፀረ አማራውን የወያኔ ፖለቲካ ከመጀመሪያው እንደታገለው ሁሉ፡፡ ፀረ ወያኔ ግንባርን ግን ለመመስረት በተካሄደው ረጅም ጥረት ኢሕአፓ የሙከራዎቹ ማዕከል ሆኖ ሲሰራ ከላይ የጠቀስናቸው ግለሰቦች-ጉዶች በሞላ ግን ወይ ህብረት መመስረቱን ሲቃወሙ ወይን በዚያን ጊዜ ወያኔን ሲያገለግሉ ነበሩ፡፡ ይህ የሚደበቅ ታሪክ አይደለም፡፡ ህብረቱ ከተመሰረተም ቀጥሎ ሳይውል ሳያድር ለፍርሻ ያደረሰው ኢሕአፓ ሳይሆን እነ ልደቱና በገንዘብ ተመክተው አፍራሽ ሚና ዛሬም የሚጫወቱት ናቸው፡፡ ችግሩ ኢሕአፓ ከሆነ ሌሎቹ እርስ በርስ ለማበር ወይም እንደተሞከረው ለመዋሀድ ለምን አቃታቸው? ውህደት ያቃታቸው በኢሕአፓ ሊያሳብቡ መመኮራቸው መሰረተ ቢስ ነው፡፡ የመኢአድና ኢዴፓ-መድህን ውህደት፤የራሱ የቅንጅቱ ችግር ያጋጠመው በራሱ ነው በኢሕአፓ? ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተባለውም ድጋፍ ያጣው ፖለቲካውና መስመሩ ለሀገር የማይበጅ ሆኖና፤የተወሰኑ የቅንጅት መሪ ነን ባዮች ከባድ ስህተትን ፈፅመው ከራሳቸው ተከታዮች ሳይቀር ጥያቄዎች በመነሳታቸው ነው፡፡ ችግር

የራሱ ባይሆን ኖሮ መላ የአማራን ህዝብ እወክላላሁ፤መላ የኦሮሞን ህዝብ እወክላላሁ የሚሉት (ያውም ኦጋዴንን ሲዳማንና ቢያንስ የአርማጨሆ ጭልጋን ህዝብ ወከልን የሚሉ ተጨምረው!) ከተባበሩ "ጠፍቷል ደክሟል" የሚባለው ኢሕአፓ እንዴት ሊያደናቅፋቸውና ሊያፈርሳቸው ይችላል?

ኢሕአፓ የብሄረሰቦችን መብት ባወቀ ሀገር አስገነጠለ ብቻ ሳይሆን የኤርትራ ግንባሮችን ሳይቀር መሰረተ ሊሉ ያልተመለሱ ጉዶች ወይም በሌላ በኩል ደግሞ ከወያኔ ጋር ሆነው ኢሕአፓ አማራውን ህዝብ ኢትዮጵያዊ ነህ ብሎ በብሄረሰብ ደረጃ እንዳይደራጅ አድርጎ አስፈጀው ባዮች ዛሬ ተባብረው ካወገዙት ሻዕቢያ ጋር መግጠም በቻ ሳይሆን በዚያድ ባሬ ጄኔራል የሚመራ ተገንጣይን ግንባርን መደገፍ ብቻ ሳይሆን ዓይን አውጥተው የሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ ሊገነጠል አልፈለገም፤ለኢትዮጵያ አንድነት የቆመ ነው ወዘተ  ብለው በድህረ ገፃቸወ ሲፅፉና ሲያስተጋቡ ለመታዘብ ደርሰናል፡፡ ያ ሁሉ ጫጫታ የት ገባ? ህብረቱ ሊመሰረት ሲል ኢሕአፓ የሻዕቢያና የዚያድ ባሬ ደጋፊ ነው፤ አትመኑት ፀረ ኢትዮጵያ ነው ብሎ ይለፍፍ የነበረው የአፍራሽ ኮሚቴ መሪ ዛሬ ምን ነክቶት የሶማሌ አክራሪዎችና የሻዕቢያ አፈ ቀላጤ ሆነ? ከአንድ የተሳሳተ ፅንፍ ወደ ሌላ በተስፈነጠረ (ዶላር? ቅዠት? አዲስ ተልዕኮ?) ለምን በኢሕአፓ ላይ ይጨፍራል? ይህ ድርጅት በከሀዲዎችና ጭንጋፎች፤ በደም አፍሳሾችና የወያኔ ቅጥረኞች መጠላቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ አልባሌ ታሪክ ያላቸው ደግሞ ገበናቸው እንዲጋለጥ አይፈልጉም፡፡ የቀይ ሽብር አራማጆች ደግሞ ኢሕአፓ ሲባል ፍርድና ቅጣት ቢታያቸው ቢያንስ ዕርቅ ሲል የቆየው ድርጅት ሀላፊ አይደለም፡፡ በድርጅቱ ላይ ወንጀል ፈፅመውና ጉዳት አድርሰው የተለዩት ደግሞ ኢሕአፓ ከጠፋ ይህ ጉዳቸው አብሮ የሚጠፋ ይመስላቸዋል፡፡ስህተት! በመሰረቱ ግን የወያኔ ዋና ጠርና ጠላት የሆነውና በዚህም የሚኮራውና የሚገፋበትን ኢሕአፓ ለማጥቃት ወያኔ ብዙ የይፋና የስውር ቅጥረኞችን አሰማርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ያነሳነው የታሪከ ጠባሳ አለ ፡፡ የፋሺስቱ ደርግ አጫፋሪዎች ዛሬም በፀረ ኢሕአፓነት ተሰማርተዋል፡፡ ሌላም አለ ፡፡ በዘመነ ደርግ በአሜሪካ ሲ አይ ኤ የተቋቋመው ኢፒዲኤ/አህዴህ / ይል እንደነበረው ኢሕአፓ ካልጠፋ "ህዝብ ማሰባሰብ" አንችልም የሚሉ አሉ፡፡ ለድክመታቸው ውስጣዊና መሰረታዊ ምክንያትን ከመፈለግ ይልቅ፤ ቀና ቢሆኑ ደግሞ ከኢሕአፓ ተመክሮ ጠቃሚ ትምህርትን ከመቅሰም ይልቅ፤ በድርጅቱ ላይ መረባረብን ይመርጣሉ፡፡ ኢዴፓ የተባለው እንደተመሰረተ ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ መጨረሻውን ዛሬ አይተናል፡፡ እነ ኢሕአፓና ሌሎችንም ያልጠቀለለ "ዴሞክራሲ" የተመኙ፤ የኢሕአፓ የታሰሩ አባላት እንዲፈቱ መጠየቅ ያመማቸው ለምን እንደበቁም ታዝበናል፡፡ በየመታጠፊያው የሚከዳው ፅናት ያለውን፤ ባንዳ አርበኛን፤ ስልጣን ጥመኛ ህዝብ አፍቃሪውን፤ ከፋፋይ ህብረት ገንቢውን፤ ወያኔው ኢሕአፓን ሊወድ አይጠበቅም፡፡

ፀረ ኢሕአፓው ዘመቻ ያልተቋረጠ ቢሆንም ለምን በሰሞኑ እየተፋፈመ መጣ? የፈረሰ ድርጅትን ግንባታ የኢሕአፓን መጠቃት ጠየቀ? ወያኔ አዘዘ ? ባዕዳን በሉ አፋፍሙ አሉ? ወይስ አንዱ የወያኔ ቅጥረኛ ከወደ አምስተርዳም ሊል እንደቃጣው ኢሕአፓ ሰራተኛውንም ሌላውንም እያደራጀ ነውና አደጋ ሆነባቸው? ወይስ አናርኪስቶች አሰጉ? አናርኮ ሲንዲካሊስቶች (አቤት ጥራዘ ነጠቅነት!) ተበራከቱ? ወይስ ሻዕቢያና የሶማሌ አክራሪዎችንና የኦነግ መሪዎችን ለማወደስ ኢሕአፓን መቀጥቀጡ አስፈላጊ ሆነ?

በዋጋ ቢስ ዘመቻው የተሰማሩት ክፍሎች መልስ እንዲሰጡ እስቲ በጋራ እንጠይቃቸው፡፡